# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

የካቲት 3 ቀን 2006 ዓ.ም

## ኢሕአፓ የሙስሊም ዜጎቻችንን ቀጣይ ትግል ይደግፋል

በመላ አዲስ አበባና ባንዳንድ ከተሞች "ትግላችን ይቀጥላል"፤ "የታሰሩት የኮሚቴያችን አባሎች ይፈቱ"፤ ...ወዘተ የሚሉ በየግድግዳው በቀለም የተጻፉ መፈክሮች የሙስሊም ኢትዮጵያውያንን ቀጣይ ትግል አብስረዋል። በተደጋጋሚ ጸረ-ወያኔ ትግላችን ይቀጥል እያለ ተመሳሳይ መፈክሮችን ሲለጥፍ የቆየው ኢሕአፓ ይህን የዜጎች እርምጃ እየደገፈ ሙስሊሞች ለመብታቸው የጀመሩትና መስዋዕት የከፈሉበት ትግል መቀጠሉን ይደግፋል።

የታሰሩትን መርሳት፤ ጥቃት ሲያይል እጅ መስጠት ለመብቱ ሊታገል ከተነሳ ሕዝብ የሚጠበቅ አይደለም። ወያኔ የሙስሊም/ዘጎችን ትግል ለማፈን ኃይል ተጠቅሟል። ቅጥረኞቹንም አሰማርቷል። ክርስቲያኖችንም አስፈራርቶ ደጋፊው ለማድረግ ያላደረገውና ያልጣረው የለም። የሙስሊም ኢትዮጵያውያንን ትግል የጽንፈኝነት ገጽታና ይዘት ለመስጠት አክራሪ ሙስሊም ሆነውና አማራና ክርስቲያን ይታረድ ብለው ብቅ ያሉ ቅጥረኞቹን መድረክ ሰጥቶ አንጫጭቷል። ሁሉም ተንኮል ግን አልሰራለትም። ሙስሊሞች ያነሱት መሠረታዊ የመብትና የዴሞክራሲ ጥያቄ፤ የወያኔን ጣልቃ ገብነት የመቃወም ጥያቄ ፍትኀዊነቱም ሊካድ የሚችል አልሆነም። ፍትኀዊና የህዝብ ድጋፍ ያለው በመሆኑም ሳይቋርጥ መቀጠል ችሏል። የወያኔ አገዛዝ ብዙዎችን አስሮና ወደ ዝዋይም አግዞ፤ በርካታዎቹን የስየል ሰለባ አድርጎና ሌሎችንም ገድሎ የፈጸመው ግፍና ወንጀል ደግሞ የሚረሳ አይደለም። በአሸባሪው ወያኔ አሸባሪ ተብለው የተከሰሱና የታገቱ ሙስሊም ዜጎች ንጹህ መሆናቸውም አከራካሪ አይደለም። ኢትዮጵያ የሁሉም ዜጎቿ ሀገር ናት-- በሃይማኖት፣ በብሔረሰብ ሆነ በጾታ ምንም ልዩነት ሊደረግ አይገባም። ዘረኛው ወያኔ ግን በሃይማኖቶች ሁሉ ጣልቃ እየገባ የፈጠረውን ችግር ሁሉም ዜጋ የሚያውቀው ነው። ኢሕአፓ ይህን ሲቃወም ቆይቷል፡ አሁንም አጥብቆ ያውግዛል።

አሸባሪውና ህገወጡ ወያኔ እንጂ ለመብቱ የሚታገለው ሕዝብ አይደለም። ኢሕአፓ የሙስሊም ዜጎችና የሁሉም ጸረ-ወያኔ ሕዝብ ትግል ይፋፋም እያለ ለሚካሄደው ትግል ያለውን ሙሉ ድጋፍ ይገልጻል።

ጸረ-ወያኔ ትግላችን ይፋፋም!


EPRP
P.O.BOX 73337
Washington DC, 20056
USA

Email ESPIC@aol.com
Website WWW.EPRP.com

EPRP
BP 22
92270 Bois Colombes
France

Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645